# ለ HUD-ድጋፍ የተደረገባቸው ተከራዮች አስፈላጊ መረጃ
# በ CDC ከቤት ማስወጣት እገዳ ላይ

ኖቬምበር 2020

ይህ በራሪ ጽሑፍ በሚከተሉት የ PIH ፕሮግራሞች፡ የቤቶች ምርጫ ቫውቸር ፕሮግራም (Housing Choice Voucher (HCV))፣ በመንግስት የቤቶች ፕሮግራም ( Public Housing program) እና በክፍል 8 መካከለኛ የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም (Section 8 Moderate Rehabilitation, Mod Rehab) ተከራዮች የሆኑ ሰዎች የ HUD-ድጋፍ የሚደረግላቸው ተከራዮች የ CDC ትእዛዝ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲረዱ በዩኤስ የቤቶች እና ከተማ ልማት ክፍል (U.S. Department of Housing and Urban Development, HUD)) በህዝባዊ እና የኢንዲያ የቤቶች ጽሕፈት ቤት (Office of Public and Indian Housing, PIH) የተዘጋጀ ነው። እርስዎ በ PIH ፕሮግራም ውስጥ ተከራይ ከሆኑ፣ እባክዎን ስለዚ በራሪ ጽሑፍ ወይም የ CDC ትእዛዝ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከአከራይዎ ወይም ከህዝባዊ የቤቶች ወኪል (PHA) ጋር ይገናኙ። እንዲሁም የ CDC ድርገጽን በ፦ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/covid-eviction-declaration.html መጎብኘት ይችላሉ።

## የ CDC ቤት የማስለቀቅ እገዳ ምንድነው?

- የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (The Centers for Disease Control and Prevention, CDC) የኮቪድ-19 ተጨማሪ ስርጭትን ለመከላከል ከመኖሪያ ቤት ማስለቀቆችን በጊዜያዊነት ማቆም (Temporary Halt in Residential Evictions ) ተብሎ የሚጠራውን ትእዛዝ አውጥቷል። የብቃት መስፈርቶችን ያሟሉ ተከራዮች፣ ይህ ትእዛዝ ***ኪራይ ባለመክፈል ከቤት ማስወጣቶችን ከሴፕቴምበር 4, 2020 እስከ ዲሴምበር 31, 2020 ለጊዜው ያቆማል***።

## የቤት ኪራይ ባለመክፈሌ ከቤት ማስወጣት ለመጠበቅ ምን ዓይነት እርምጃዎችን መውሰድ አለብኝ?

- **እርምጃ 1**፦ እርስዎ ከአከራይዎ ወይም ከPHA ጋር ያለመክፈል ሁኔታ ውስጥ ከሆኑ እና ከሴፕቴምበር 4, 2020 እስከ ዲሴምበር 31, 2020 ቤት የማስለቀቅ አደጋ ላይ ከሆኑ፣ በ CDC ሰነድ ውስጥ ያሉ ከታች የሚገኙ ሁሉምንም ሰባት የምስክር ወረቀቶች ማሟላት **አለብዎ**። እዚህ ይገኛሉ፦
  - **እንግሊዝኛስሪት፦** https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/downloads/declaration-form.pdf
  - **የተተረጎሙ እትሞች፦** https://www.hud.gov/program_offices/public_indian_housing/covid_19_resources/resident_declaration_form-other_languages
- **እርምጃ2**፦ በ CDC አዋጁ ውስጥ ሁሉምንም ሰባት የምስክር ወረቀቶች ካሟሉ፣ ከዚያ ሰነዱን ፈርመው ቀን ማድረግ ይኖርብዎታል።
- **እርምጃ3**፦ ለእርስዎ PHA ወይም አከራይ የተፈረመበት/ቀን የተጻፈበት የአዋጁ ቅጂ ይስጡ።

## እርምጃ 1: በመጀመሪያ በCDC አዋጁ ውስጥ ሁሉምንም ሰባት ምስክር ወረቀቶች ማሟላት አለብዎ። እነሱም፦

1. **በቤተሰብ ገቢ መቀነስ ወይም ያልታሰበ የህክምና ወጪዎች ምክንያት ሙሉውን ኪራይ መክፈል የማይችሉ ከሆነ፤**
   - **ጠቃሚ ምክር**! ለ መንግስት ቤት ተሳታፊዎች እና የቫውቸር ተሳታፊዎች፣ የገቢዎ ለውጥ ለእርስዎ PHA ሪፖርት ካደረጉ ኪራይዎ የገቢዎን መቀነስ ለማንጸባረቅ **ሁልጊዜ** ይስተካከላል። እባክዎን የአሁኑ ገቢዎን ለመከለስ እና ለውጡን እንዲያንጸባርቅ ኪራይዎን ለማስተካከል ወዲያውኑ የእርስዎን PHA ያግኙ።

2. **ሁኔታዎች እስከሚፈቅዱ ድረስ ለሙሉ ክፍያ ሊጠጋጋ የሚችል ከፊል ክፍያዎችን በጊዜው ለማድረግ የሚቻልዎትን ጥረት እያደረጉ መሆኑን።**

3. **ሁሉም የሚገኘውን የመንግስት ድጋፍ ለማግኘት የተቻልዎትን ጥረቶች ማድረግዎ።**
   - **ጠቃሚ ምክር!** የመንግስት ድጋፍን ለማግኘት የተቻልዎትን ጥረት ማድረግዎን ለመወሰን በኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም ውስጥ የአሁን ተሳታፊነትዎን ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላሉ። የመንግስት የቤት ተሳታፊዎች እና የቫውቸር ተሳታፊዎች የአሁን ገቢያቸውን እንዲገመግም እና በገቢያቸው ውስጥ ለውጥእንዲጸባረቅ ኪራዩን ለማስተካከል PHA ን ከጠየቁ ግምት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ።

4. **ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱን ያሟላሉ፦ (1) በ 2020 ከ $99,000 (ወይም $198,000 በጋራ ፋይል ካስገቡ) ያነስ ለማግኘት ይጠብቃሉ፣ ወይም (2) ማንኛውንም ገቢ ለ IRS ሪፖርት ማድረግ ያልተጠየቁ ከሆኑ ወይም (3) የኮሮና ቫይረስ ድጋፍ፣ አስቸኳይ እርዳታ እና የኢኮኖሚ ዋስትና (Coronavirus Aid, Relief, and Economic Security, CARES) ሕግ የማነቃቂያ ቼክ ከተቀበሉ።**
   - **ጠቃሚ ምክር**! የ $1,200+ የማነቃቂያ ክፍያው በገቢዎ ስሌት ውስጥ አልተካተተም። የማነቃቂያ ክፍያ ካልደረስዎ፣ እባክዎን የክፍያዎን ሁኔታ ለመፈተሽ ይህንን የድርገጽ ይጎብኙ እና ቀላል ቅጽ ይሙሉ፡ https://www.irs.gov/coronavirus/get-my-payment

5. **ቤት እንዲለቁ የሚደረጉ ከሆነ፣ ቤት አልባ የመሆን ወይም ወደ ቤት አልባ መጠለያ የመሄድ ዕድል አልዎት ወይም በተጋሩ የተጠጋጉ ቤቶች ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመኖር ወደ አዲስ ቤት መሄድ ይችላሉ።**

6. **ያልተከፈለ ክራይ መክፈል ኃላፊነትዎ እንደሆነ፣ ላልተከፈለ ኪራይ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ሊጠየቁ እንደሚችሉ እና የኪራይዎን ውሎች ማክበር መቀጠል እንዳለብዎ ይረዳሉ።**

7. **የ CDC ትእዛዝ ዲሴምበር 31, 2020 በሚያበቃበት ጊዜ፣ ያልተከፈለ ኪራይ ወይም ያልተከፈሉ ክፍያዎች ካለብዎት ቤት እንዲለቁ ሊደረጉ እንደሚችሉ ይረዳሉ።**

## እርምጃ 2፦ ሁሉንም ሰባት ምስክር ወረቀቶች ካሟሉ በእርምጃ 1 ውስጥ ሰነዱ ላይ ፊርማ እና ቀን ያኑሩ።

- በእርምጃ 1 ውስጥ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟላ በኪራዩ፣ የኪራይ ስምምነቱ ወይም የቤቶች ኮንትራት ላይ የተዘረዘረ እያንዳንዱ አዋቂ ሰነዱን መፈረም አለበት። በአንዳንድ ሁኔታዎች እንደ ውስጥ የጋራ የታክስ ተመላሽ ፋይል ያስገቡ ግለሰቦች፣ የቤተሰብ አንድ አባል በሌሎች አዋቂ ነዋሪዎች ምትክ በችግር ላይ በኪራዩ፣ የኪራይ ስምምነቱ ወይም የቤት ኮንትራቱ ላይ የተፈጸመ ሰነድ ማቅረብ ተገቢ ሊሆን ይችላል። እዚህ ያለውን የ CDC አዋጅ መጠቀም ይችላሉ፡ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/downloads/declaration-form.pdf.

## እርምጃ 3፦ ለእርስዎ አከራይ ወይም ለ PHA የተፈረመበት የሰነዱ ቅጂ ይስጡ።

- **አስፈላጊ!** ሰነዱን ለአከራይዎ ወይም ለPHA ፈርመው ካለስረከቡ፣ ከሴፕቴምበር 4, 2020 እስከ ዲሴምበር 31, 2020 መሃከል ኪራይ ባለመክፈልዎ ከቤት እንዲለቁ ሊደረጉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በሐሰት የመመስከር ቅጣት መስረት ሰነዱ የመረጃ እውነተኛነት እንዲያረጋግጡ ይፈልጋል። ይህ ማለት ማንኛውም ሃሰተኛ ወይም የሚያሳስቱ መግለጫዎች ወይም ማስቀረቶች የገንዘብ ቅጣት፣ መቀጮዎች፣ ጉዳቶች ወይም እስር የመሳሰሉ የወንጀለኛ እና የፍትሃብሄር እርምጃዎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፣ ስለዚህ **እባክዎን ሰነዱ ላይ ከመፈረምዎ በፊት በእርምጃ 1 ያሉ ሁሉንም የምስክር ወረቀቶች ማሟላትዎን ያረጋግጡ።**
- ኪራይ ባለመክፈል ቤት ማስለቀቁ ከሴፕቴምበር 4 በፊት ከጀመረ ሆኖም ግን እስከ አሁን ገና ካልተጠናቀቀ፣ ከቤት ማስወጣቱን ለመከላከል ስነዱን ፈርመው ለአከራይዎ ወይም ለPHA ማቅረብ ይችላሉ።
- ከተቻለ፣ መላክዎትን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ በሚሰጥ መንገድ ሰነዱን በኢሜይል ወይም በሌላ ስልት በኩል ይላኩ። ለምሳሌ፣ ሌላ ስልት በዩኤስ የፖስታ አገልግሎት በኩል የተመላሽ ደረሰኝ የተጠየቀበት የተረጋገጠ ደብዳቤ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ወደ አከራይዎ ወይም PHA የተላከበት ወይም የደረሰበት ቀን እና ሰዓት አካቶ ለመዝገብዎ የተፈረመ ሰነድ(ዎች) ቅጂ ይያዙ።
- የቫውቸር ተሳታፊዎች እንዲሁ ለእርስዎ PHA እና ለአከራይዎ ሰነድዱን ሊሰጡ ሊፈልጉ ይችላሉ።

## እባክዎ ልብ ይበሉ፦

- ኪራይዎን መክፈል ወይም ከፊል የኪራይ ክፍያዎችን መክፈል ከቻሉ፣ አሁንም እንደሱ ማድረግ ያስፈልግዎታል።
- በ CDC ትእዛዝ ውስጥ ያለው ከቤት የማስወጣት እገዳ አሁን ካበቃው ከ CARES ሕግ[1] ውስጥ ካለው ከቤት የማስወጣት እገዳ የተለየ ነው። በ CARES ሕግ ውስጥ ከቤት የማስወጣት እገዳው የሚያበቃው ጁላይ 24, 2020። በሁለቱም መሃከል ያለው ከፍተኛው ልዩነት፣ በ CDC ተእዛዝመሰረት፦ (1) ተከራዮች ኪራይ ባለመክፈላቸው ምክንያት ቤት እንዲለቀ ከመደረግ እንዲጠበቁ በሁሉም ሰባት የምስክር ወረቀቶች ሰነድ ላይ መፈረም ያስፈልጋቸዋል እንዲሁም (2) ተከራዮች ባልተከፈለ ኪራይ ምክንያት ለዘገዩ ክፍያዎች፣ ቅጣቶች እና ሌሎች ክፍያዎች ሊቀጡ ይችላሉ።
- የእርስዎ ስቴት፣ አካባቢ ወይም ግዛት ባለስልጣን ረጅም ወይም በ CDC ትእዛዝ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ተመሳሳይ ወይም የበለጠ ደረጃ ያለው የህዝብ-ጤና ጥበቃ የሚሰጡ ከቤት ማስወጣቶች ላይ ተጨማሪ አሳሪ እገዳ የጣሉ ሌሎች ጥበቃዎች ሊኖሩዎት ይችላሉ።
- ሁሉንም የኪራይዎን ውሎች እና የሚኖሩበትን አካባቢ ደንቦች አሁንም መከተል ያስፈልግዎታል። ለወንጀል ተግባሮች፣ ለሌሎች ተግባሮች ወይም ለኪራይ ጥሰቶች ተከራዮች አሁንም ቤት እንዲለቁ ሊደረጉ ይችላሉ።

## ከእርስዎ አከራይ ወይም PHA ጋር የመገናኘት ጠቃሚ ምክሮች፦

ኪራይ ለመክፈል እየተቸገሩ ከሆነ ወይም መክፈል የማይችሉ ከሆነ፣ አማራጮችዎን ለመወያየት አከራይዎን ወዲያውኑ ያነጋግሩ። በአስጨናቂ የፋይናንስ ጊዜያት ወቅት፣ አከራይዎም እንዲሁ ተግዳሮቶች ሊኖሩት ይችላሉ። ከእነሱ ጋር በግልጽ እና ረጋ ብለው ለማናገር ይሞክሩ። ከአከራይዎ ጋር በሚያደርጉት ንግግር ሊያግዝዎት የሚችሉ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች ይኸውልዎት፦

- ስለ ሁኔታዎ ግልጽ ይሁኑ። በኮቪድ-19 ወይም በሌሎች ችግሮች የተጠቁ ከሆኑ፣ ገቢዎ ምን ያህል እንደተጎዳ ያጋሩዋቸው። የመንግስት የቤት ተሳታፊዎች እና የቫውቸር ተሳታፊዎች የአሁን ገቢዎ ለመገምገም እና የኪራይዎ ክፍያ ለማስተካከል በተቻለ መጠን ከእርስዎ PHA ጋር መነጋገር ይገባቸዋል።
- ያገኙትን ማንኛውንም ሃብቶች እና የድጋፍ አማራጮች መጥቀስን ግምት ውስጥ ያስገቡ።
- በቤት ማጣት ምክንያት ምን ያህል ቤተሰብዎ እንደሚጎዳ ይግለጹ።
- ስለ ክፍያ ዝግጅቶች ይጠይቁ።
- ማንኛውንም የኢሜይል እና የጽሑፍ ውይይቶችን ይጠብቁዋቸው እንዲሁም በስልክ ወይም በአካል መቼ እንደተነጋገሩ ማስታወሻ ይያዙ።

---

[1] በኮሮና ቫይረስ እገዛ፣አስቸኳይ ድጋፍ እና የኢኮኖሚ ዋስትና ሕግ፣ 2020 የ “CARES Act” (መንግስታዊ ሕግ 116-136) በክፍል 4024 ውስጥ የተደነገገ።